# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter
Published by the Public Relations and Communication Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-10 የጥር ወር 2010 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-10 January, 2018 G.C




## የአመራር ፎረም አባላት የቡሬ ካምፓስ የግንባታ ስራዎችን ጎበኙ

- የመሰረተ ልማት ሥራዎችን ለማሟላት ጨረታ የማውጣት ስራ እየተሰራ ይገኛል፤
- ግንባታው በ956 ቀናት ተጠናቅቋል፤
- ግንባታው የመማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች ዶርምተሪ እና መመገቢያ አዳራሽ ያካትታ፤
- በሶስት ዓይነት አማራጭ የሀይል ምንጮች የተሟሉለት ነው፡፡
- ግንባታዎች ጥራታቸውን የጠበቁ ከመሆናቸው ባሻገር ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡
- እስካሁን ድረስ ለግንባታው ከ374 ሚሊዮን ብር ወጭ ተደርጓል፡፡

## በውስጥ ገፆቻችን


- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 182 ሰዎች ደም ለገሱ........4
- የህክምና ት/ቤት ለኢንተርንሺፕ ለሚወጡ ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ተሰጠ...6
- የሴት ተመራማሪዎችን አቅም በማሳደግ ችግር ፈች ጥናቶችን መስራት እንደሚቻል ተገለፀ....7
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በምዕ/ጐጃም ዞን ለሚገኘው ጐህ ህብረት ስራ ዩኒየን የሰጠው ስልጠና ችግር ፈች እንደነበር ሰልጣኞች ገለፁ...9
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር እብጠት በሽታን ለመከላከል ከዞኑ ጤና መምሪያና ጤና መድህን ጋር ስምምነት አደረገ.......11
- የተማሪዎችን መረጃ አያያዝ ለማዘመን ስልጠና ተሠጠ ..............13
- የሰላም ፎረም ለመማር ማስተማር ሥራው ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ተገለፀ......... 14
- ለተማሪዎች አለመረጋጋት መንስኤ ለሚሆኑ ጉዳዮች መፍትሔ መስጠት እንደሚገባ ተገለፀ......... 15
- የ2ኛ ዲግሪ ተማሪዎች መመረቂያ ጽሁፎች የማህበረሠቡን ችግር ሊፈቱ በሚችል መልኩ መዘጋጀት እንዳለባቸው ተገለፀ .........17
- የአመራር ፎረም አባላት የቡሬ ካምፓስ የግንባታ ስራዎችን ጎበኙ ........18
- DMU Medicine students take Comprehensive Exit Exam ..............20
- 182 Persons Donate Blood at DMU ……21
- Debre Markos University works intensively on Podoconoisis……….22
- Training held for Female Researchers…..24
- Peace Forum brings remarkable achievements on pedagogical process…..25
- **DMU provides Training for Gohe Farmers' Cooperative Union at West Gojjam…….. 26**
- **DMU Develops New SIMS …………28**



09-13-88-63-49 **Fax. 058-771-17-64**
✉ **269** dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

## ራዕይ
## Vision

እ.ኤ.አ. በ2025 ከአፍሪካ 10 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

**Debre Markos University strives to be one of the top ten Universties in Africa by 2025.**

## ተልዕኮ
## Mission

ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

**Producing competent, ethical and innovative graduates through providing quality instructional, Co-curricular and cultural involvement.**

አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

**Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders at local and national levels.**

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

**Providing demand driven community and consultancy services that contribute to the national development objectives.**



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እየተዘጋጀች ለአንባብያን የምትደርሰው ወርሃዊ ዜና መጽሔት በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተካሄዱ የተለያዩ ሁነቶችን ዘገባ፣ የዩኒቨርሲቲውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ሌሎች ቁምነገሮችን አካታ ለንባብ ስትበቃ ቆይታለች፡፡

በዚህ እትም የጥር ወር 2010 ዓ.ም. ዜና መጽሔታችን በዩኒቨርሲቲው የተደረጉ ውይይቶችን በስፋት ዳሳለች፡፡ መልካም ንባብ!

ለወርሃዊ ዜና መጽሔታችን መሻሻል የእናንተ የአንባቢያን አስተያየት ወሳኝ በመሆኑ ለሚኖራችሁ ማንኛውም አስተያየት

በድረ ገጽ www.dmu.edu.et ወይም



09-13-88-63-49 **Fax. 058-771-17-64** ✉ **269** dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 182 ሰዎች ደም ለገሱ

በወርቅነሽ ደመም



የደም ልገሳ ፕሮግራም በከፊል

በደም እጦት የሚሰቃዩ ወገኖችን ለመታደግ እንደሚሠራ የደብረ ማርቆስ ደም ባንክ አገልግሎት ተገለፀ፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከደብረ ማርቆስ የደም ባንክ አገልግሎት ጋር በመተባበር የማህበረሰቡን ህይወት ለመታደግ ባዘጋጀው የ5 ቀን የደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ 182 የዩኒቨርሲቲው አካላት ደም ለገሱ፡፡

የደም ልገሳው ዓላማ የደብረ ማርቆስ የደም ባንክ አገልግሎት ደም የሚያስፈልጋቸውን ብዙ ደም የሚፈሳቸው ወላድ እናቶች፣ ከፍተኛ ቀዶ ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች፣ ሲወለዱ ደም ለሚያንሳቸው ህፃናትና ለመሳሰሉት ህሙማን ከበጐ ፈቃደኞች ጥራቱን የጠበቀ ደም በማሰባሰብ በነፃ ለማሠራጨት እንደሆነ የደብረ ማርቆስ ደም ባንክ አገልግሎት ባለሙያ አቶ አብርሃም አበባው አብራርተዋል፡፡

የደም ልገሳ ስራውን የበለጠ ለማቀላጠፍ የደብረ ማርቆስ ደም ባንክ አገልግሎት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የህይወት ጠብታ የሚባል ክበብ በማቋቋም ከ40 በላይ ለሚሆኑ

የክበቡ አባል ተማሪዎች ስልጠና በመስጠት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ ግንዛቤ ኖሮት እንዲሳተፍ ለማድረግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ አድርጓል፡፡

የደም ልገሳ በሚደረግበት ወቅት ማንኛውም ሰው ደም ከመለገሱ በፊት እድሜው ከ18 ዓመት እስከ 65 ዓመት፣ ክብደቱ ከ45 ኪ.ግ በላይ፣ በደም ከሚተላለፍ በሽታዎች ነፃ የሆነ፣ በጐ ፈቃደኛና ሙሉ ጤነኛ መሆኑ እንደሚረጋገጥ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነፍሰ ጡር እናቶች፣ የሚያጠቡ እናቶችና የተለያዩ መድሀኒቶችን በመውሰድ ላይ ያሉ ሰዎች ግን ደም መለገስ እንደማይችሉ ተገልጿል፡፡

የደብረ ማርቆስ የደም ባንክ አገልግሎት በአማራ ክልል ከሚገኙት ስድስት የደም ባንኮች አንዱ ሲሆን ከተለያዩ የትምህርት ተቋማትና ከመሳሰሉት በነፃ የተሰበሰበውን ንፁህ ደም ደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል ጨምሮ ለ14 ሆስፒታሎች በነፃ እያሠራጨ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በደብረ ማርቆስ የደም ባንክ አገልግሎት የሚደረገው የደም ልገሳ እንደ ሌሎች አካባቢዎች የተጠናከረ ባይሆንም አሁን በተሻለ መልኩ ተደራጅቶ በጥሩ ሁኔታ እየሠራ እንደሆነና ለወደፊት ከዚህ በበለጠ ተጠናክሮ እንደሚሠራ የደም ባንክ አገልግሎት ባለሙያው አብራርተዋል፡፡

ይህ የደም ልገሳ ፕሮግራም ከ2005 ዓ.ም. በፊት በቀይ መስቀል ይካሄድ የነበረ ቢሆንም የሚለገሰው ደም በቂ ባለመሆኑ ከዚያ ዓመት ጀምሮ የጤና ጥበቃ የደም ባንኮችን በማቋቋም በደም ባንክ አገልግሎት ደም እንዲለገስ ተደርጓል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ከህይወት ጠብታ ክበብ አባላት በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ወደ ደም ባንክ አገልግሎት በመሄድ የደም ልገሳ እንዲያደርግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ቢያደርግ ሲሉ ባለሙያው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የህክምና ት/ቤት ለኢንተርንሺፕ ለሚወጡ ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ተሰጠ

በወርቅነሽ ደመም



በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በህክምና ት/ቤት ከ4ኛ ዓመት ወደ 5ኛ ዓመት የገቡ የህክምና ተማሪዎች ወደ ተግባር ልምምድ (Internship) ከመሄዳቸው በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፈተና (qualification exam) ተሰጠ፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በህክምና ት/ቤት ለተማሪዎች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ዋና አላማው ተማሪዎቹ በቀጣይ በደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል ለሚያደርጉት የኢንተርንሺፕ ቆይታ ብቁ ሆነው በሌሎች ሀኪሞች ስር በመሆን በሽተኞቻቸውን ማከም መቻል አለመቻላቸውን ለማረጋገጥ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡ ፈተናው የተሠጠው በዩኒቨርሲቲው በሚያስተምሩ መምህራንና ከውጭ በመጡ ሐኪሞች እንደሆነ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ት/ቤት የህፃናት ህክምና ትምህርት ክፍል ተጠሪ ዶ/ር ኤርሚያስ አበባው አብራርተዋል፡፡

የብቃት ማረጋገጫውን የተፈተኑ የህክምና ተማሪዎች በቂ ውጤት ባያመጡና በአንድ የትምህርት አይነት ቢወድቁ የወደቁበትን የትምህርት ዓይነት ለ7 ሣምንታት ደግመው በመማር በዩኒቨርሲቲው መምህራን ፈተና ተሰጥቷቸው ወደ ተግባር ልምምድ ይገባሉ፡፡ የወደቁባቸው የትምህርት ዓይነቶች ሁለትና ከዚያ በላይ ከሆኑ ግን ዓመቱን በሙሉ በመድገም ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች እንደሚማሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ለህክምና ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያስፈልገው በ4 ዓመት ቆይታቸው በንድፈ ሃሣብ (theory) ያገኙትን ዕውቀት በልምምድ ወደ ተግባር ለመቀየር ለማስቻልና ብቁ ሆነው እንዲወጡ ለማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በአጠቃላይ 13 ሳምንታትን በተግባር ልምምድ የሚቆዩ ተማሪዎች አንድ ሳምንት የዕረፍት ጊዜያቸው ሆኖ ሌሎቹ 12 ሳምንታት ግን የተግባር ልምምድ የሚያደርጉባቸው ጊዜያት ናቸው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ቤት መምህራን ለልምምድ የወጡ ተማሪዎችን ባዘጋጁት መስፈርት መሠረት በመገምገም 6 ወር ሲሞላቸው ያሳዩትን ጥንካሬ፣ የጨበጡትን ክህሎትና መስተካከል ያለባቸውን ነጥቦች በተመለከተ ለተማሪዎች ግብረ መልስ እንደሚሰጧቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በ13ኛው ሳምንት መጨረሻ ደግሞ ተማሪዎችን በድጋሚ በመጥራት በ6ኛው ሳምንት የተሰጣቸውን ግብረ መልስ መሠረት አድርገው ያሣዩትን ለውጥ ይገመግማሉ፤ በሚደረገው ክትትል በተግባር ልምምዱ ብቁ ሆነው ካልተገኙ እንደገና በልምምዱ እንዲቀጥሉ እንደሚደረግ ዶ/ር ኤርሚያስ ተናግረዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ተማሪዎች ከተግባር ልምምድ ቆይታቸው በኋላ ሙያው የሚፈልገውን ክህሎት፣ ዕውቀትና አመለካከት በመጨበጥ እንዲሁም በጥሩ ሥነ ምግባር ታንፀው እንደሚወጡ ይጠበቃል ሲሉ ዶ/ር ኤርሚያስ አክለው ገልፀዋል፡፡

## የሴት ተመራማሪዎችን አቅም በማሳደግ ችግር ፈች ጥናቶችን መስራት እንደሚቻል ተገለፀ

በወርቅነሽ ደመም



የስልጠናው ከፊል ገፅታ



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የሴቶችን አቅም ለመገንባት የ2ኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ ላላቸው ሴት መምህራን በምርምር ትልመ ጥናት አፃፃፍ እና በምርምር ውጤት አተናተን ዙሪያ የ3 ቀን ስልጠና ተሰጠ፡፡

የስልጠናው ዓላማም ቁጥራጨው ዝቅተኛ የሆነውን የሴት ተመራማሪዎችን ቁጥር ለመጨመር፣ አቅም ለማሳደግ እና ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት እንደሆነ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ አብራርተዋል፡፡

የስልጠናው ይዘቶች የምርምር ትልመ ጥናት አፃፃፍ፣ የምርምር ውጤት አተናተን እና በውስጡ መካተት ያለባቸውን ነገሮች የያዘ ሲሆን አንድ ተመራማሪ የምርምር ትልመ ጥናቱን ለማዘጋጀትም ሆነ ምርምሩን ለመስራት በጥልቀት ማሰብ መቻል እንዳለበት ስልጠናው የሠጡት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ከፍተኛ ተመራማሪ አቶ አበበ ቅሩብ ገልፀዋል፡፡

አንድ ተመራማሪ ምርምሩን የሚሰራው ደረጃውን ከፍ ለማድረግ፣ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት አሊያም ደግሞ ፈንድ ለማፈላለግ ታስቦ ሲሆን የሚሠሩ ምርምሮችም ሳይንሳዊ፣ ቴክኖሎጂ መር፣ የንግድና ፖለቲካዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ ተመራማሪው የተለያዩ ቴክኒኮችን ተጠቅሞ የሠራውን ምርምር ማን፣ ለምን፣ መቼ፣ የት እና እንዴት የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ መተንተን መቻል እንዳለበትና የተገኘው ውጤትም ሁሉም የመጨረሻ ውጤት ሊሆን ስለማይችሉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውን በመምረጥ የሚያመጣውን ለውጥ ማየት እንደሚገባው ተብራርቷል፡፡

የአንድ ጥናት አነሳስ ችግሮችን /Statement of the problem/ ለመለየት እንደ መስፈርት ሆነው የሚያገለግሉ የተመራማሪው ፍላጐት፣ ምርምሩ ሲሰራ የሚሰጠው ጠቀሜታ፣ አዋጭነቱና የመሳሰሉት ሲሆኑ ትልመ ጥናቱ እና የምርምር ጽሑፉ የሚያካትታቸው መሠረታዊ ነጥቦችም በሰፊው ተዘርዝረዋል፡፡ ከምርምሩ በኋላ የምርምር ወረቀቱ በሚፃፍበት ጊዜ እና የምርምር ጽሑፉን ለማሳተም መደረግ ያለባቸውን ቅደም ተከተሎችና ሊጠነቀቋቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በተመለከተም በስልጠናው ይዘት ውስጥ ተጠናክሮ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ ስልጠናው የምርምር ትልመ ጥናት ከማዘጋጀት አንስቶ የምርምር ወረቀቱን ማሳተም እስኪችል ድረስ መደረግ ያለባቸውንና መካተት የሚገባቸውን መሠረታዊ ነጥቦች፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና የመፍትሔ ሃሳቦችን ጠቅለል አድርጐ የያዘ እንደሆነ በመግለጽ ለሌሎችም የማዳረስ ሥራ መሰራት እንዳለበት የስልጠናው ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በምዕ/ጐጃም ዞን ለሚገኘው ጐህ ህብረት ስራ ዩኒየን የሰጠው ስልጠና ችግር ፈች እንደነበር ሰልጣኞች ገለፁ

በእንደሻው ያዛቸው



የስልጠናው ክፊል

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በጐህ የገንዘብ ቁጠባና በድር ህብረት ስራ ዩኒየን ለታቀፉ አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠና ሰጠ፡፡ ስልጠናው ከወንበርማ፣ ሰከላ፣ ቡሬ ወረዳና ቡሬ ከተማ አስተዳደር ለተወጣጡ 62 የሚደርሱ የህብረት ስራ አመራሮች እና 50 ባለሙያዎች በሁለት ዙር በቡሬ ከተማ ተሠጥቷል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የስልጠናና ማማከር መኮነን አቶ ባሳዝነው ድረስ በስልጠናው ወቅት እንደተናገሩት በጐህ የህብረት ስራ ዩኒየን ውስጥ የሚካሄደውን የአሠራር ስልት ቃኝቶ በዩኒየኑ ውስጥ ከሚገኙት የህብረት ስራ ማህበራት የተገኘውን ልምድ በመለዋወጥ አሠራሩን ለማዘመን ወጥ የማህበራት የስራ እንቅስቃሴ እንዲኖር በሚል ዓላማ የተዘጋጀ ስልጠና ነው ብለዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቡሬ ግቢ ዲን አቶ ጠግቤው ዋለ በበኩላቸው ቡሬ ግቢ በተመሠረተበት ከ2006 ዓ.ም. ጀምሮ በመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ብዙ ስራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ አስታውሰው በይበልጥም ፍላጐትን መሠረት ያደረገ የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ስር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እየሠጠ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በዚህም ረገድ ጐህ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ዩኒየን



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

እምቅ እውቀት ከሚገኝበት ቡሬ ግቢ በጠየቁት የስልጠና ፍላጎት መሠረት አሠልጣኞች በምጣኔ ሀብት፣ በገንዘብ አያያዝ እና አስተዳደር በሚሉ ይዘቶች ዙሪያ ስልጠና እንደተሠጠ ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ዘላቂ የህብረት ስራ ማህበራት አመራር ጽንሰ ሀሳብና ትርጉም ስልት በመምህር ዘመኑ አማረ፣ የፋይናንስ ስራ አመራርና የቁጠባ ምንነት በመምህርት አብዩ ጌቴ እና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራት ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ትስስር በመምህርት ታደለ አለምነህ የቡሬ ግቢ መምህራን ስልጠናው እንደተሠጠ ታውቋል፡፡

በውይይቱም ወቅት በተለያዩ ማህበራት ውስጥ የሚስተዋሉትን የቸልተኝነት፣ የሰው ኃይል መዋቅር ችግር፣ የቅጥር ሰራተኞች የብቃት ችግር፣ የአመራር፣ የድጋፍ፣ የክትትልና ቁርጠኝነት ችግሮች እንደነበሩ ሰልጣኞች አንስተዋል፡፡ በቀጣይም መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ቁጠባዎችን በመቆጠብ፣ የአባላትን ቁጥር ለማሳደግ፣ የገንዘብ ብድርንና አመላለስ ስርዓትን ለማዘመን የማህበራቱን ብሎም የዩኒየኑን ዕድገት ዘላቂነትና አጠቃላይ ህልውና ማሳደግ መቻል እንዳለባቸው አንስተዋል፡፡ ለዚህም ነጋዴዎች፣ ደንበኞች፣ ተጠቃሚዎች፣ የገንዘብ አንቀሳቃሾች፣ ትርፍ ተከፋዮች ራሳቸው የማህበሩ አባላት በመሆናቸው የኃላፊዎችን ብቃት ለማሳደግ፣ በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ለማነጽ ጉልህ ሚና እንዳለው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የተሟላ የሠው ኃይል መዋቅር በመጠቀም የገንዘብ ወጭንና ገቢን በአግባቡና በተደራጀ መልኩ በመያዝና በመመዝገብ፣ አመራሩም ከላይ እስከታች የማህበሩን እንቅስቃሴ በተሻለ መልኩ በማደራጀት፣ በማስፋፋትና በመከታተል ውጤታማ ማድረግ እንዳለባቸው ሰልጣኞች አሳስበዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር እብጠት በሽታን ለመከላከል ከዞኑ ጤና መምሪያና ጤና መድህን ጋር ስምምነት አደረገ

በእንደሻው ያዛቸው



አቶ አብዮት ሞላ
የማህበረሰብ ልማት መኮነን

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከእርዳታ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የእግር እብጠት በሽታን ለመከላከል በምስራቅ ጐጃም ዞን ስር በሚገኙ ስናን ወረዳ ረቡ ገበያ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ እና ጐዛምን ወረዳ አባሊባኖስ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ለረጅም ጊዜ ስራውን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም ዘርፍ ከ78 በላይ ታካሚዎች በከፍተኛ ደረጃ ከህመማቸው የተፈወሡ መሆኑን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ልማት መኮነን አቶ አብዮት ሞላ ገልፀዋል፡፡

በደብር ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ምህረት ዓለማየሁ በበኩላቸው ረጅ ድርጅቶች በባለፈው ዓመት የነበራቸውን የኮንትራት ስራ ጨርሰው ስራውን እንዲያስቀጥሉ ሲሠሩባቸው ለነበሩት ክሊኒኮች በማሳወቅ ወጥተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በስራቸው ወቅት በነበራቸው ቆይታ 86%



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በበሽታው የተያዙትን ሠዎች ከህመማቸው በመፈወስ ውጤታማና አበረታች እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡

ይሁን እንጅ በሽታው በይዘቱ አስከፊ በመሆኑ፣ በሽተኞች ከማህበረሰቡ በመገለላቸውና በእንቅስቃሴያቸው ደከም ያሉ በመሆናቸው፣ ማህበረሰቡ ለበሽታው ያለው ዝቅተኛ አመለካከት እንዲሁም ህክምናው ለህክምና ባለሙያዎች አስቸጋሪ በመሆኑ ስራው በተወሠነ መልኩ የተፋዘዘ ቢሆንም ስራውን ግን እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የቀድሞ ረጅ ድርጅቶች ስራቸውን ጨርሰው ሲወጡ ስራውን ለማስቀጠል ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከዞኑ ጤና መምሪያና ጤና መድህን ኤጀንሲ ጋር በጋራ በመወያየት ሶስቱ ተቋማት ተባብረው ለመስራት ከስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ስራውንም በቅርብ ጊዜ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡

ለዚህም የጤና መድህን የድሀ ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎች በሁሉም ወረዳዎች 10% ነፃ የህክምና አገልግሎት ይሠጣል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የጤና መምሪያው የድሀ ድሃ የሚባሉትንና በበሽታው የተያዙትን ግለሠቦች መረጃዉ ተጠንቶና ተሠብስቦ እንዲመጣለት ለወረዳዎች ተልዕኮ ሠጥቷል፡፡

ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው፣ ጤና መምሪያውና የጤና መድህን ተቋማት በጋራ በመተባበር ከዚህ በፊት ከሰራባቸው ሁለት ወረዳዎች በተጨማሪ በሁሉም የዞኑ ወረዳዎች በቀጣይ ውጤቱም ታይቶ በምዕ/ጐጃም ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ጭምር እንደሚሠሩ በስምምነቱ ወቅት ተገልጿል፡፡

በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው ያለው የጤና ኮሌጅ ሙያውን ተግባራዊ እንዲያደርግ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በዩኒቨርሲቲው ስር ሆኖ የማስተባበር ስራውን እንዲሠራና ጤና መምሪያውና ጤና መድህኑም የራሳቸው የስራ ድርሻ እንዲወስዱ ስምምነት ላይ መደረሱን ዶ/ር ምህረት ገልፀዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የተማሪዎችን መረጃ አያያዝ ለማዘመን ስልጠና ተሠጠ

*በስማቸው አየነው*



የስልጠናው ከፊል ገፅታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ዳይሬክቶሬት ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተግበር የተማሪዎችን መረጃ አያያዝ ለማዘመን በተሰራው ሶፍትዌር (Students' Information Management System) ለመምህራን ለአምስት ተከታታይ ቀናት ስልጠና ተሠጠ፡፡

የሬጅስትራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ሁነኛው ደሴ ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው የአንደኛ አመት ተማሪዎችን ኮርስ የሚሠጡ ሁሉም መምህራን እንዲሠለጥኑ የተደረገ ሲሆን ዋና አላማው የተማሪዎች መረጃ አያያዝ ማኑዋል በመሆኑ እና ይህን ለማስቀረት የመረጃ አያያዝ ለማዘመን በማሠብ እንደተዘጋጀ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም ስልጠናው በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች የተሠጠ ሲሆን ባለድርሻ አካላት ስልጠናውን እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ በቀጣይም ወደ ተግባር ለመግባት የክትትል ስራ እና የኢንተርኔት አገልግሎት የማስፋት ስራ እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡ ይህን የመረጃ አያያዝ እንዲዘመን ማድረጉ መምህራንን ቀጥታ ያለስጋት ለተማሪዎች ውጤታቸውን ለማሳወቅ እንዲሁም ተማሪዎች ውጤታቸውን ጊዜ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የኢንተርኔት አገልግሎት ባለበት ቦታ ሁሉ እንዲያዩ እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ተወካይ ዳይሬክተር አቶ ጋሻው በልስቲ በበኩላቸው የስልጠናው ዋና አላማ የተማሪዎች መረጃ ኤሌክትሮኒካል በሆነ መልኩ እንዲቀመጥ ማድረግ ሲሆን የተማሪዎች መረጃ አስተዳደር የተማሪዎችን መረጃ በዘመናዊ መልኩ የሚይዝ ሲስተም በመሆኑ ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ በተለይም ደግሞ ጊዜን በመቆጠብ፣ የመረጃ አያያዝ ስጋትን በመቀነስና መሠረታዊ እና ዘመናዊ በማድረግ ከጠቀሜታዎች ውስጥ የተወሡኑት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ስራው ተግባራዊ እንደሆነም በዳይሬክቶሬቱ አንድ ኦፊሠር መድበው እንዲተገበር የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም ሲስተሙ አዲስ እንደመሆኑ መጠን በደንብ የተደራጀ ማዕከል እንዲኖረው ቢደረግና ተጨማሪ ባለሙያና አስፈላጊ ግብአቶች እንዲሟሉ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው አመራር አባላት ትኩረት እንዲሠጡት አሳስበዋል፡፡

## የሰላም ፎረም ለመማር ማስተማር ሥራው ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ተገለፀ

*በስማቸው አየነው*



ተማሪ እሸቴ ምህረት
የደ/ማ/ዩ/ የሠላም ፎረም ሠብሳቢ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሠላም ፎረም የመማር ማስተማሩ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ገለፀ፡፡ የፎረሙ ሠብሳቢ ተማሪ እሸቴ ምህረት እንደገለፀው የሠላም ፎረሙ የተቋቋመው በዋናነት በዩኒቨርሲቲው ውስጥና አካባቢ ሠላም እንዲሠፍን የግጭት መንስኤዎችን በመለየትና አለመግባባቶችን በመፍታት ችግሮች እንዳይከሠቱ የመከላከል ስራ በመስራት ችግሮች ሠላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት እንዲቻል መሆኑን አስረድቷል፡፡



09-13-88-63-49 **Fax. 058-771-17-64** ✉ **269** dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሠላም ፎረም በግቢው ውስጥ ተገልጋይ ማህበረሠቦችን ቅድሚያ በማወያየት፣ የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በውይይት የመፍታት፤ መቻቻል እንዲሠፍን የማድረግ፣ የማስታረቅ፤ በዲሲፕሊን ምክንያት የሚባረሩ ተማሪዎችን ቁጥር የመቀነስ እና መሠል ተግባራትን እያከናወነ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ እንዲሁም ከሌሎች አደረጃጀቶች ጋር በመቀናጀት የሠላም ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራትን አስቀድሞ የመለየትና የመፍታት ስራ እንደሚሠራ ገልጿል፡፡

ፎረሙ ከተማሪዎች ከመምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች የተውጣጡ 16 አባላትን የያዘ ሲሆን በየሳምንቱ አርብ በመገናኘት የተሠሩ ሥራዎችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችን እና መሠራት የሚገባቸውን ተግባራት በጋራ ይገመግማል፤ የመፍትሔ አቅጣጫም ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መሠረት ያለመግባባት ችግር መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለይቶ ቅድሚያ የመምከርና የማስተካከል ስራ እየሠራ ለመማር ማስተማሩ ሥራ ጉልህ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ አስገንዝቧል፡፡ በቀጣይም ፎረሙ ለግቢው ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎች በመጠቀም ግንዛቤ ለመፍጠር እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ተማሪ እሸቴ ምህረት ገልጿል፡፡

## ለተማሪዎች አለመረጋጋት መንስኤ ለሚሆኑ ጉዳዮች መፍትሔ መስጠት እንደሚገባ ተገለፀ

*በስማቸው አየነው*



**አቶ ታደሰ ጤናው**
**የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት**



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በታህሳስ ወር ተከሰቶ የነበረው የተማሪዎች አለመረጋጋት ሙሉ በሙሉ ወደ ሠላም መመለሡና ወደፊት እንዳይከሠት መንስኤ ለሚሆኑ ጉዳዮች መፍትሔ መስጠት ተገቢ መሆኑ ተገለፀ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት አቶ ታደሠ ጤናው በዩኒቨርሲቲው ተከስቶ በነበረው አለመረጋጋት የመማር ማስተማሩ ሥራ ለ3 ተከታታይ ቀናት ተቋርጦ እንደነበር በማስታወስ ለአለመረጋጋቱ ምክንያትም በዋናነት በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተከስቶ የነበረው አለመረጋጋት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተከሠተውን ችግር የዩኒቨርሲቲው አመራር አካላትና መምህራን ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር ወደ ነበረበት ሁኔታ የመመለስ ስራ ሰርተዋል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎች ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

አቶ ታደሰ ጤናው አያይዘውም የተረጋጋ ሠላም አለመኖሩ ደግሞ በተማሪዎች ላይ ጫና ከመፍጠር ባሻገር ለትምህርት ጥራቱም ከፍተኛ እንቅፋት እንደሆነና የተቋረጡት የትምህርት ቀናት በማኔጅመንት በመወሠን መምህራን በማካካሻ ፕሮግራም እንዲያካክሱ ከማድረግ በተጨማሪም የትምህርት ካሌንደሩን በመከለስ እንዲስተካከል የማድረግ ሥራ እንደተሠራ ገልፀዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር አባትሁን አለኸኝ በበኩላቸው ሠላም ባለመኖሩ ምክንያት ተማሪዎች የስነልቦና አለመረጋጋት፣ ለመማር ዝግጁ አለመሆን፣ ወደ ክፍል አለመግባት እና ተረጋግቶ አለማንበብ ተከስቶ እንደነበር በዚህ ደግሞ ኮርሶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይሸፈኑ ስለሚያደርግ በት/ት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው አብራርተዋል፡፡ ስለዚህ የትምህርት ካሌንደር ተከልሶ ከነበረው የ4 ቀናት ጭማሬ ተደርጐ ኮርሶች እንዲሸፈኑ እንደተደረገ እና መምህራን በየትምህር ክፍሎች ተማሪዎችን የመምከርና የማረጋጋት ሥራ መስራታቸውን ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም ወደፊት እንደነዚህ አይነት ችግሮች እንዳይፈፀሙ የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች እና የማስገንዘብ ስራ መሥራት ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የ2ኛ ዲግሪ ተማሪዎች መመረቂያ ጽሁፎች የማህበረሠቡን ችግር ሊፈቱ በሚችል መልኩ መዘጋጀት እንዳለባቸው ተገለፀ

*በስማቸው አየነው*




ተማሪዎች ተቋቁሞ ሲያቀረቡ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ 87 ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውን አቀረቡ፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር አሐዱ መንዝር በአሁኑ ሠዓት በዩኒቨርሲቲው በ37 የትምህርት መስኮች 2913 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች በመደበኛው፣ በማታውና በክረምት መርሀ ግብሮች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ እንደሚገኙ ገልፀው በ9 የትምህርት መስኮች ከጥር ወር 2010 ዓ.ም. የመመረቂያ ጽሁፋቸውን እንዲያቀርቡ የተደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የመመረቂያ ጽሁፍ ዋና ዓላማ የማስተርስ ድግሪውን ለማግኘት በከፊል መስፈርት መሆኑ እና የአካባቢውን ማህበረሠብ ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ጥናቶች እንዲዘጋጁ ለማድረግ ሲሆን ሁሉም የሚሰሩ የምርምር ጽሁፎች በዚህ መልኩ መዘጋጀታቸውን የመከታተል እና ወደ ፕሮጀክት እንዲቀይሩ የማድረግ ክፍተት እንዳለ አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም የተማሪዎችን ሥራ በተገቢው መልኩ ሠንዶ በመያዝ ለማጣቀሻነት እንዲያገለግሉ የማድረግ ሥራ የሚፈለገውን ያህል ትኩረት ባይሠጠውም የተሻሉ ጽሁፎችን ግን በቤት

መጽሐፍት እንዲቀመጡ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ጥሩ መመረቂያ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ አንጋፋ መምህራንን በአማካሪነት በመመደብ የማገዝና የመደገፍ ሥራ በሠፊው እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ወደፊትም የመመረቂያ ጽሁፎች በዩኒቨርስቲው የምርምር የትኩረት አቅጣጫ መሠረት እንዲዘጋጁ እና ከሌላ ሠው ሥራ ተቀድተው እንዳይቀርቡ ትኩረት ሠጥተው እንደሚሠሩ ጠቁመዋል፡፡

የጥናት ጽሁፍ ያቀረቡት ተመራቂ ተማሪዎች በበኩላቸው የተመደቡላቸው አማካሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ሲያደርጉላቸው እንደነበር በመግለጽ ያቀረቧቸውን ጽሁፎች የመጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ እና ተጨማሪ ማስተካከያዎች በማድረግ የማሳተምና እውቅና እንዲያገኙ የማድረግ ስራ እንደሚሠሩ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም በቀጣይ ዩኒቨርሲቲው በአማካሪነት የሚመድባቸው መምህራን ተገቢውን እገዛ እንዲያደርጉ ክትትል የማድረግና መመረቂያ ጽሁፎች በደንብ ተሠንደው እንዲያዙ የማድረግ ስራ እንዲሠራ ጠቁመዋል፡፡

## የአመራር ፎረም አባላት የቡሬ ካምፓስ የግንባታ ስራዎችን ጎበኙ

*በስማቸው አየነው*



የጉብኝቱ ከፊል ገፅታ



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ የህንፃ ግንባታዎች የስራ እንቅስቃሴ በዩኒቨርሲቲው የአመራር ፎረም አባላት ተጎበኘ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ ልማት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳይህ ካሳው የጉብኝቱን ዓላማ ሲያስረዱ በመገንባት ላይ ያሉ አስራ አንድ ህንፃዎችን የአማካሪ ድርጅቱ ስራ አስኪያጅና የተቋራጭ ድርጅቱ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ በተገኙበት ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት ጉብኝት መደረጉ በአመራር ፎረሙ አባላት አስተያየት ተሰጥቶበት የታዩ ችግሮች ካሉ ከወዲሁ ለማስተካከል እንዲያመች መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም ህንፃዎቹ ስራ ከመጀመራቸው በፊት መሰረተ ልማት ለማሟላት ጨረታ የማውጣት ስራ እየተሰራ መሆኑና በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ስራ እንደሚጀምር ገልፀዋል፡፡

በጉብኝቱ ወቅት የአማካሪ ድርጅቱ አማካሪ መሀንዲስ አቶ ዮናስ ሙሉሰው ለተሳታፊዎች የግንባታውን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ በሪፖርቱም ግንባታው በ956 ቀናት እንደተጠናቀቀ በመግለፅ ግንባታው የመማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች ዶርምተሪ እና መመገቢያ አዳራሽ እንደያዘና ሶስት ዓይነት አማራጭ የሀይል ምንጮች የተሟሉ ሲሆን ጥራታቸውን የጠበቁ ከመሆናቸው ባሻገር ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው እንደተሰሩ አስረድተዋል፡፡ እስካሁን ድረስም ለግንባታው ከ374 ሚሊዮን ብር ወጭ ተደርጓል በማለት ተናግረዋል፡፡ ቀሪ ስራ የማፅዳት ስራ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ርክክቡ እንደሚካሄድ አቶ ዮናስ ተናግረዋል፡፡

ተሳታፊዎች በበኩላቸው የሳይት ወርክ ስራ፣ የሶላር መሳሪዎች አቀማመጥና የመሰረተ ልማት ስራዎች አለመሟላት የሚታዩ ችግሮች እንደሆኑ ጥያቄ ያነሱ ሲሆን አማካሪ መሀንዲሱ አቶ ዮናስ ሙሉሰው ከተቋራጭ ድርጅቱ ጋር በመነጋገር የማስተካከል ስራ የሚሰራ ሲሆን የሳይት ስራ ግን በአዲስ ውል ስለሚሰራና የውሉ አካል ስላልነበረ እንዳልተጠናቀቀ አብራርቷል፡፡

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች ግንባታው በጥሩ ሁኔታ እንደተከናወነ ገልፀው ያልተጠናቀቁ ስራዎች በቶሎ ቢጠናቀቁና በመማሪያ ክፍሎች የውሃ አገልግሎትና የመፀዳጃ አገልግሎት እንዲሁም ስራ ከመጀመሩ በፊት የግቢ ዋና ዋና መንገዶች እንዲሟሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

## DMU Medicine students take Comprehensive Exit Exam

Debre Markos University School of Medical has given comprehensive exit exam (also known as qualification exam) for fifth year medicine students before joining clinical internship. In line with this, the head of department of epidemiology Dr. Ermiyas Abebaw remarks that the basic intention of the exam is to identify students who are capable of doing their anticipated practical activities in Debre Markos Referral Hospital.

The exam has administered and invigilated by the school teachers and external physicians. In doing so, the students have checked as they are capable enough to treat patients besides other physicians.

Furthermore, the internship is considered as a comprehensive tool to enable students exploits the theoretical knowledge they got during their four years study and execute into practice. This finally could make them efficient and capable of doing every activity practically.

Hence, the internship is for 13 consecutive weeks it is expected to bring change on the students' clinical viewpoints. In doing so, Debre Markos University School of medicine teachers will supervise the students and provide relevant and adequate feedback for the sake of improvement. Hence, the teachers will conduct a general overview on the students' progress and capability as to how they are effectively addressed the clinical internship objectives.

As a matter of fact, all students are not supposed to join the internship class unless they are fulfilling the courses requirement. This means, a student who did not score pass grade within a single subject, he must enrolled for the course and learn for 7 weeks again and take re-exam through their teachers. Nevertheless, if the students fail more



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

than a subject, they would take all the subjects throughout the year. Therefore, passing or qualifying in courses is a criterion to the internship.

Finally, Dr. Ermiyas remarks that Medicine students are expected to be skillful, knowledgeable and ethical to handle the internship program properly, legally and honestly and then make themselves ready to serve the community.

# 182 Persons Donate Blood at DMU



Debre Markos blood bank service inn association with Debre Markos University organizes five days blood donation program at the University from January 24-28/2018. During the program, 182 persons donate blood to the blood bank.

Debre Markos blood bank service expert Mr. Abraham Abebaw explains that the objective of blood donation was to provide pure blood from volunteers to highly vulnerable individuals such as mothers during delivery, for high level of surgeon, babies with blood shortage when they are born and others. It was noticed that the blood donation was conducted upon the status of individuals whose age is between 18-65 years, 49 kg weigh and above, with the good will of donors. However, pregnant



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

women, breast feeder women and patients who take medicine do not the part donations.

Hence, being one of the sixth blood banks found in Amhara Region, Debre Markos blood bank service is distributing blood for 14 hospitals including Debre Markos Referral Hospital without any payment. Thus, the blood is collected from different nearby educational institutions and volunteers.

The blood donation service was provided via Red Cross society before 2013, since then, it is moderately activated in blood bank services organized by health care institutions. Nowadays, Debre Markos blood bank service is doing its level best deeds than ever before. In this regard, Debre Markos University community is also doing remarkable achievements on donating blood. In order to facilitate the blood donation service at Debre Markos University Life Droplets /'Yehiwot tebita' students' club plays a pivotal role. In line with this, more than 40 students from the club have taken training regarding on blood donation so as to create awareness for the university community.

## Debre Markos University works intensively on Podoconoisis




**Mr. Abiyot Molla**
**Community development officer**



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

Debre Markos University the directorate of Community service intensively works on curing of Podoconoisis at East Gojjam Zone woredas. Debre Marko University community development officer, Mr. Abiyot Molla states that the University has worked long times now with different donors and non-government organizations to cure podoconoisis. It was spatially functional in Sinan woreda, Rebugebeya and Gozamin woreda Abalibanos health care centers. Thus, more than 78 patients have been treated from their high-level illness of the disease.

On the other hand, Debre Markos University Community Service Directorate Director Dr. Mihret Alemayehu elaborates that donors and non-government organizations have finished their agreement on podoconoisis curing and prevention project. They have given to the former health centers to let the treatment continue so far. Thus, it was 86% effective of curing the patients from their fierce illness. However, because of the blunt nature of the disease, the patients are stigmatized from the community. Low awareness, perceptions, attitudes and other related reasons were some of the reasons to overlook the distribution of the disease.

Nonetheless, as the termination date of the term of reference of donors and non-governments organizations, Debre Markos University again carrying out the project in collaboration with zone health department and health insurance institutions. The university is strongly keen to discuss on the issue of podoconoisis with the zone health department and health insurance to endorse the service at health centers and let the service continue much better than before.

Hence, the health insurance institution agreed to offer 10% free services for needy groups. In doing that, the zonal health departments are working endlessly to gather reliable information and truly screening of the needy groups and the diseased ones engaged entirely from each woreda. Therefore, this cooperation consolidated the service to cure podoconoisis from the entire woredas in Eastern and, if possible, western Gojjam Zone Woredas.

# Training held for Female Researchers





Sr. Genet Degu, Delivering Opening speech

Debre Markos University research and technology transfer directorate trains female researchers to build their ability on effective way of conducting research. The training contents on proposal writing, research findings and interpretations.

The Vice president for Research and Community Service Assistant Professor Genet Degu in her welcoming speech states that the objective of the training is increasing the number of female researchers and maximizing their ability of doing research as well as filling the gaps of conducting thematic researches underneath.

The trainer is Dr. Abebe Kirub, a senior researcher in Ethiopian agricultural research center. Dr Abebe states that conducting research proposals profoundly should be taken as part and parcel of individuals' life in academic world in order to seek solutions of every problem. He also tells that the essence of proposal writing, ways of research finding analysis, interpretation and communication was the contents of the training they have to develop in their professional endeavor. Rationally, elevating grace of experts, solving communities' problems and/or designing fund raising projects are the concern of conducting academic research. Cognizant this, the research results are to be



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

disseminate for scientific, technology leading, merchandise and political incentives /inputs through employing special techniques in response of questions like what, way, when, where and how questions to address substantial results beneath it.

Points regarding on setting statement of the problem as it emanated from the interest of the researcher, significance of the research, effectiveness and other sub research genres are enumerated during the training.

# Peace Forum brings remarkable achievements on pedagogical process



Student Eshetie Mihret
DMU Peace forum Chairperson

Debre Markos University peace forum, one of the student organizations in the University, is fundamental for significant in keeping and maintaining peace in teaching learning activities.

The forum Chairperson student Eshetie Mihret states that peace forum is established to create peaceful internal and external learning environment after analyzing and



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

identifying the causative agents of conflicts through proactive conflict resolution mechanisms.

Debre Markos University peace forum adheres peaceful co-existence through discussing the University's Community primarily on solving disagreements through peaceful ways; performing tolerance and respect, arbitrating of conflicts, minimizing and lately avoiding students who commit mistakes in the university. In addition to this, the forum works on forming strong linkage among several arrangements so that prevent causes of problems easily to live mutually peaceful in an intercultural setting.

The forum consists of 16 members from students, teachers and administrative staff members drawn rationally. These members are usually conducting reasonable summits to talk over activities and identify challenges and difficulties occurred in the university to plan anticipated activities so that put concrete directives and remedies for the risks.

Thus, individuals could live together in harmony and become strong for overcoming unexpected problems, which may occur accidentally and ultimately brings positive change on the holistic teaching-learning activities.

## DMU provides Training for Gohe Farmers' Cooperative Union at West Gojjam



Partial view of the training



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

Debre Markos University the Directorate of Community service provides training on Strategic operation of cooperative business for Gohe farmers' Cooperative Union, which is found at Burie. 50 trainees from Womberma, Sekela, Burie and Burie Surrounding Woredas are the participants of the training.

During the training, training and consultancy officer in the directorate of community service Mr. Basazinew Dires states that Gohe Farmers' Cooperative Union is currently working in a conventional way that needs transformation to a modern cooperative business operation.

On the occasion, the dean of Burie campus Mr. Tegbew Walle explains that as Burie campus provides community based services in teaching, research and community service since its establishment as a campus of Debre Markos University in 2013. Particularly, community services are organized for the surrounding community upon their interests and needs. Mr. Tegbew adds that the training organized at Burie aims at improving the Union's financial and management capabilities.

The Gohe Farmers' Cooperative Union has face problems. Some of the problems are incompetent structure, lack of qualified human power, leadership faults, lack of commitment and weak monitoring system. In general, the cooperative business needs improvement in a holistic management skill in each structure to maintain their services adequately.

Thus, the cooperative needs conceptual understanding and implementation on the sustainable management periodically. The contents of the training are Cooperative business operation and finance management and saving habit that are given by Mr. Zemenu Amare and Mrs. Abiyu Gete respectively. In addition to these, Mr. Tadele Alamneh trains on partnership and linkage of unions with saving & credit financial institutions.

# DMU Develops New Student Information Management System



The registrar directorate of Debre Markos University implements the newly developed SIMS on 2010 entry students. In order to utilize the system the directorate organizes training sessions for academic staffs. The system makes the students' information highly secured via maintaining supervision and control mechanisms at different levels.

The director of the registrar directorate Dr. Hunegnaw Dessie states that the newly developed Student Information Management System (SIMS) is vital to completely change traditional paper work student information recording system in to simple, computerized and highly secured system.

The training participants are teachers who have courses for first year students while the trainers are from Information Communication Technology Directorate. The acting director of ICT Mr. Gashaw Belsti on his part states that as the system has crucial for students and teachers or the university as a whole in saving time, rescue threats and cost minimizing. According to Mr. Gashaw, in order to make the system software accessible by all teachers it has to consolidate the internet service besides the training.



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et